## **ጠላቶቹን በሚገባ የተረዳው አማራ!** በአዲስ ተስፋ

ካለፈው የቀጠለ

በቅርብ ጊዜ አማራን በተመለከተ ያለኝን የማይናወጥ አቋም በፌስ ብክ ገጼ ባስተዋወቅሁበት መጣጥፌ አንድ ወዳጄ እንዲህ ሲል መከረኝ። ‘’ በየካቲት 12 አብርሐም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም (ሁለቱም በአሁኑ እይታ ኤርትራውያን ናቸው) በግራዚያኒ ላይ ቦንብ ጥለው ሲያቆስሉት ፣ የጣሊያን ፋሺስቶች የወሰዱት እርምጃ "አማራንና የኦርቶዶክስ ካህናትን ግደሉ" የሚል የሰቆቃ ትእዛዝ ነበር። ስለዚህ ይህ ጣሊያናዊ  አስተሳሰብ  (አማራውንና ኦርቶዶክስን ማጥፋት የሚለው ) ዘመናትን ሁሉ ተሻግሮ እስከዛሬ ድረስ የምስኪኖች ደም እንዲፈስ ምክንያት ሆኗል። ስለዚህ ኢትዮጵያ አገራችን በዜግነት ክብር ላይ የተመሠረተ መንግሥት እስክትመሠርትና የዘር ፖለቲካ እስኪቆም ዐማራውም የሚወክለው የራሱ የሆነ ሕብረት ቢኖረው እኔም መልካም ነው እላለሁ። ከዚህ ጋር ግን መረሳት የሌለበት የዐማራው ብሔርተኝነት ለሌሎች ብሔሮች ስጋትን የሚፈጥር መሆን የለበትም። በተጨማሪም አሁን በዶ/ር አብይ የሚመራውንም ለውጥ ማደናቀፍ የለበትም። በለውጡ ውስጥ የዐማራውን ድምጽ ግን ማሰማት አለበት። ስለዚህ አንተም ወንድሜ  እውነትንና ፍት ህን መሠረትህ አድርገህ በፍቅርና በሰላም እስከታገልክ ድረስ አሳብህን አበረታታለሁ። ለተጨቆኑ፣ ለተገፉ፣ ለሚሳደዱና በግፍ ለተጠሉ መቆም ተገቢ ነው። ሌላው መረሳት የሌለበት በአማራው ክልል የሚኖሩ የሌሎች ብሔሮች ሰዎች ነፃነታቸውና መብታቸው ተጠብቆ በሰላም መኖር አለባቸው። የበቀል ፖለቲካ ክፋ ታሪክ ሆኖ በታሪክ መመዝገቡ ብቻ ሳይሆን ውጤትም አይኖረውም።’’ በማለት ታሪክን አጣቅሶ መቀላቀል አለብኝ ስላልኩት አማራን የመታደግ ትግል ድጋፉን ገለጸልኝ። በእርግጥ የ አማራና ኦርቶዶክስ ጥላቻ ከዚያም የቀደመ ታሪክ አለው። ወራሪዎች ምስራቅ አፍሪካን በተለይም ኢትዮጵያን አላስነካም ብሎ ደምና አጥንቱን የገበረውን ይህንን ማህበረሰብ አይወዱትም። የሚገርመው እነዚህ ጠላቶቻችን ከመካከላችን ባንዳዎችን መግዛት መቻላቸው ነው። ከጥንትም ጀምሮ በአቃፊነቱና በአስተዳደር ብቃቱ የተመሰከረለትን ይሕንን ህዝብ ለማጥፋት በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል አሁንም በመሰራት ላይ ይገኛሉ። ለዚህም በርካታ አብነቶችን መጥቀስ ብቻ ሳይሆን ከበቂ በላይ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል። ጓደኛየ የዶክተር አብይን የለውጥ ሂደትም መደገፍ ይገባል ብሏል። ምክሩ እንዳለ ሆኖ እስኪ ዛሬም እየተሰራ ያለዉን ግፍ እንመልከት። የኢትዮያ ሶማሊያ ክልል በሚባለው የተደረገውን የቅርብ ጊዜ ግፍ መነሻውንም መድረሻውንም ብንመለከት በማንም ሳይሆን በአማራ ህዝብ ላይ ያነጣጠረ ነበር። በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ስለግድያውና ዝርፊያው አስተያየት የሚሰጡ ግለሰቦችን በማየት ብቻ ለዚህ ምስክርነት መስጠት ይቻላል። መነሻውን ብንመለከት ከአመታት በፊት ሾልኮ ወጣ በተባለ መረጃ ቀድሞ ፕሬዚደንት በነበረው አብዲ ኢሌ እና የሶማሊያ ሽማግሌዎች መካከል በተደረገ ውይይት መዋጋት የሚገባቸው አማራን ብቻ እንድሆነ ያሳሰባቸው ነበር። አማራ ጠላት እንደሆን ቀድሞውኑ ለአካባቢው ሰው ተነግሯል። የሶማሊያን ግርግር  አጠቃላይ በክልሉ የሚኖሩ ከሌላ ክልል የመጡ ሰዎችን ለማስዎጣት የተደረገ ነው ለማስባልና ይህንንም ሚዲያዎች በቀላሉ እንዲዘግቡት ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ ነበር። ለዚህ ማደናገሪያ ይሆን ዘንድ መከላከያ ክልሉን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጠረው ከተባለ በኋላ ከአርባ በላይ ኦሮሞዎች ከምስራቅ ሃረርጌ ተጨፈጨፉ ተባለ። እንዴት ና ለምን?ብለን መጠየቅ አለብን።አብዲ ኢሌ አደራጃቸው የተባሉ ወጣቶችም ይሁኑ ልዩ ሃይሉ የተዘጋጀው አማራን ለማጽዳት ፣ በአማራ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመፈጸም ነበር። አሁን ነገሩ ሁሉ የተገለጠለትን አማራውን ማታላል እማይቻልበት ደረጃ ላይ መድረሱ መልካም መሆኑ እንዳለ ሆኖ አሁንም ያልነቁና በህዝባቸው ላይ የሚደረገው ሽፍጥ ያልገባቸው እንዳሉ ግን መካድ አይቻልም። ከላይ እንደጠቀስኩት ጓደኛየ  ‘’ አማራና ኦርቶዶክስን ለማጥፋት ’’ ከጥንት ጀምሮ የነበረው አላማ አሁንም ገና አልተቋጨም። እንደገና ወደሶማሊያው እልቂት እንመለስ። በጅግጅጋም ይሁን በሌሎች የክልሉ ከተሞች በተደረገው ግድያ፤ዝርፊያና ድብደባ ተጎጅ የነበረው ከዘጠና በመቶ በላይ አማራው ነበር። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ መኮነን የተባለ አክቲቪስት በ18/08/2018  በሰራው የማህበራዊ ሚድያ ቪድዮ አሁን መንግስት ለተጎጂዎች እርዳታ እየሰጠ ባለበት ሁኔታ ተጠቃሚዎች የተፈናቀሉ አማሮች ሳይሆኑ አፈናቃዮች ራሳቸው ተሰልፈው እርዳታ እየውሰዱ እንደሆነ ተናግሯል።

አላማው ግቡን ገና አልመታም። አማሮች ወጥተው አላለቁም ስለዚህም ማማረሩና ማስመረሩ ይቀጥላል። ሌላው ተያያዡና ቀጣዩ ኢላማ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን መሆኑ ነው። ከአስር በላይ የሆኑ በተክርስቲያናት በሁለትና ሶስት ቀናት ብቻ መውደም ማለት በትክክል የሚነግረን አይኑን ያፈጠጠ እውነት አለ። እዚህ ላይ ይህንን አረመኔያዊ ድርጊት ለማውገዝና በቃ ለማለት ኦርቶዶክስ መሆን አያስፈልግም። ኦርቶዶክስ ኢላማ የሆነችው ልክ እንደ አማራው ሁሉ አንድ አገር በማለቷ ብቻ ነው። አንድ አገር ማለት አንድ ባንዲራ ማለት ለውጭ ጠላቶቻችን እምቢ አልገዛም ማለት ነው። ይህንን የተመለከቱ ባእዳን እነ አብዲ ኢሌን ብቻ ሳይሆን በርካታ አብዲ ኢሌዎችን አሰማርተውብናል። አማራውም ከመቼውም ጊዜ በተለየ መልኩ ጠላቶቹን ተረድቷቸዋል። የተማማሉበትን አውቋቸዋል። ልዚህም ነው አያ ጅቦ ሳታመኻኝ ብላኝ በማለት ላይ የሚገኘው። የህወሃት ወንጀለኛ መሪዎችም  የተነሳሳውን የ አማራን ህዝብ ትግል ለማዳፈን ፣ ስነ ትኩረታችን ወደለሎች አቅጣጫዎች እንዲበታተን ለማድረግ ብዙ ስራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ። ለምሳሌ ለማህበራዊ ሚዲያው የተለያዩ ትኩረት የሚስቡ የቤት ስራዎችን በመስጠት እርስ በእርሳችን አንድንከራከር በማድረግ ተኩረታችንን ለመስረቅ እየሰሩ ይገኛሉ። ለምሳሌ ትግሉ ተቀልብሷል አልተቀለበሰም የሚሉ ርእሶች፣ ይህወሃት መሪዎች በአደባባይ አብይን ሰድቡ በማለትና ሌሎችንም ሰሞነኛ ወሬ ለቃቃሚዎች እንድንሆን በማድረግ ስራቸውን መቀጠል። አማራንና ኦርቶዶክስን ከእንግዲህ ቢያንስ በማታለል ወደ ፊት መራመድ እንደማይቻል ጠላቶቻችን ማወቅ ይኖርባቸዋል።  አማራ ከሚታሰበው በላይ አጥፊዎቹንም መሪዎቹንም እያወቃቸውና የራሱን እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል። የዶክተር አብይን የለውጥ ሂደት መደገፍና አለመደገፍ ለአማራው የሚበጀው ነው ብሎ ብዚህ ሰዓት መደምደም ፋይዳው እምብዛም ነው። በመሰረቱ ዶክተር አብይ በአማራ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል አልተሰራም

ብለው በአደባባይ ተናግረዋል። ይህ ደግሞ ዓላም የተቀበለውን እውነት መካድ ብቻ ሳይሆን ሆ ብሎ ድጋፍ የሰጣቸውን ያንን ምስኪን የአማራ ህዝብ በቁስሉ እንጨትም መስደድ ነው።

ምንም እንኳ በአማራነት ስለመደራጀት ባላቸው አመለካከት በተወሰኑቱ ባልስማማም አቶ ተስፋየ ደጉ የባሉ ሰው በፌስብክ ገጻቸው

" በአገራችን ላለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት እንደ አማራው የተደራጀና የተቀናጀ ጥቃት ሰለባ የሆነ ማህበረሰብ ያለ አይመስለኝም ። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት በህወሓት ፊታውራሪነት በተደራጁት የዘውግ ድርጅቶች ማህበረሰቡ እንደ ጨቋኝና ገዥ በመበየኑ የጥቃት ሰለባ ሲሆን በተደጋጋሚ ተስተውሏል ። በዘውግ ተደራጅቶ አማራውን እንደ ጠላት የማያይ የፖለቲካ ድርጅት በውርርድ እንኳን የሚገኝ አይመስለኝም ።አሁን አሁን ለፖለቲካ ግብ በአማራነት መደራጀትን የሚደግፉ የአማራ ልሂቃን በርከት ብለው ይታያሉ ። አማራው በመገፋቱና ማቆሚያ ያለው በማይመስል ደረጃ የጥቃት ሰለባ በመሆኑ የደረሱበት ውሳኔ በመሆኑ ብዙም ላይገርም ይችላል" ይላሉ። እኚህ ሰው የገባቸውን አንድ እውነት ማጉላት ቢያስፈልግ በራሳቸው ቃላቶች "አማራው በመገፋቱና ማቆሚያ ያለው በማይመስል ደረጃ የጥቃት ሰለባ በመሆኑ" በማለት ገልጸውታል።

የአማራው ጥቃት መቆሚያ ያለው አይደለም። ይህንን እውነት ደግሞ ጠላቶቻችን ብቻ ሳይሆኑ አሁን አሁን ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችም እየተረዱትና እየተገነዘቡት ይገኛሉ። ሌላው ቀርቶ የፖለቲካ ድርጅቶች የጥንካሬያቸው መስፈርት ጸረ አማራ መሆን ነው። ከለይ ከጅምሩ መጥቀስ እንደሞከርኩት ይህ ጥልቅ የሆነ ጸረ አማራ ህብረተሰብ መገንባት ለፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ፍንትው ብሎ ስለታያቸው ነበር አማራን የማዳን መረጃዎችን ለኢትዮጵያ ህዝብ ማስተላለፍ የጀመሩት።

ፕሮፌሰር አስራት በጀመሩት ጎዳና ለመቀጠል የሞከሩ ሁሉ በየደረጃው በተዘጋጀው የማጥፋትና የውግዘት ሰንሰለት የኢትዮጵያ ህዝብ ሊረዳው በማይችል የተቀነባበረ ኢላማ ሲመቱ ኖረዋል። ኢንጅነር ሃይሉ ሻውል አንደኛው ሰለባ ነበሩ። ኢንጅነር ሀይሉ ሻዎልን ጠልፎ የጣለው ቀጥታ በመንግስት ውስጥ የተዘረጋው ጸረ አማራ ማዋቅር አልነበረም። ይልቁንም  በእስር ቤት እያሉ የትግል አጋሮቼ በሚሏቸውና እቅድ ለ በሆነው የተቃዋሚ ጎራ በተሰገሰጉ ከሃዲዎች ነብር። እንዲያውም በአደባባይ የትግራይ ፈላጭ ቆራጮችን አስዎግጄ የአማራ ፈላጭ ቆራጭ ለማምጣት አልታገልም በማለት ዶክተር ብርሃኑ አላገጠባቸው። ይህንን እውነት የአማራ ልሂቃን ብቻ ሳይሆኑ እያንዳንዱ ተራ ህዝብ የተገነዘብበት ወቅት ላይ ደርሰናል። በምርምሩ አለም ችግርህን ማዎቅ ሃምሳ በመቶ መፍትሄውን እንዳገኘኸው ይቆጠራል የሚል ጠንካራ እምነት አለ።ስለዚህም ለአማራ የሚቆረቆሩ ወደ ፊት ሲመጡ ተጠልፈው የሚዎድቁበት ምክን ያት በዘመናት ሁሉ ተግባራዊ ሲደረግ ለቆየው ጸረ አማራ ፖልቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሂደት ግብዓት ነበር። ኢንጅነር ሃይሉ በፕሮፌሰር አስራት መሰረቱ የተጣለውን እውነትና የህዝብ ፍላጎት ይዘው በመነሳታቸውም ዘረኛውን አገዛዝ ከስሩ አፋለሱት ፤ በሃሰትና በደባ ይጎመራውን ዘረኝነትም በህዝባቸው ሃይል ገነደሱት። በዚህ የተቆጣውና እንደቆሰለ አውሬ የሆነው በህወሃት የሚመራው አምባ ገነን በቀጥታ በእስር ከማሰቃየት በተጨማሪ ጓደኛ መስለው በቀረቧቸው ባልደረቦቻቸው ፖለቲካዊ ደባ ፈጸሙባቸው። ይሄም በቀጥታ አማራውን አደንቁሮና አደህይቶ የመግዛት እቅድ ነበር። ይህ ሁሉ ሲሆን ጠላቶቹን ሲያጎርስ የኖረው የአማራ ህዝብ ገንዘቡና ጉልበቱን ለሚያጠፉት ነገር ግን ወኪልህ ነኝ ለሚሉት ጠላቶቹ  ሲገፈግፍ ኖረ። ክህደትን እስከሚበቃው ተጎነጨ።  በዶክተር ታየ ወልደስማያት የተፈጸመው ሻጠርም ተመሳሳይ ነበር። የሚገርመው እስካሁን የተመለከትነው በተቃዋሚው ጎራ አማራ እንዴት እየተጠለፈ እንደወደቀ ሲሆን በራሱ በገዥው መደብ የአገዛዝ ስንስርለት ወስጥ ያሉትም አማራ በመሆናቸው ብቻ እየታደኑ አስቀድሞ መጠቀሚያ ከሆኑ በሁዋላ እንዲገደሉ እንዲታሰሩና እንዲሰደዱ ይሆን ነበር።  ለዚህም አስቀድሞ የህዝብ ግንኙነት ስራ ይሰራባቸዋል። በህዝብ ስነልቦና ውስጥ ሌቦች እንደሆኑ ወይም ጠላት እንደሆኑ በመንገር ምንም አይነት ጥያቄ እንዳይነሳ ይደረጋል። ከዚያም አማራን የማጽዳት ዘመቻ ይካሄዳል። እዚህ ላይ እስኪ ሁለት አብነቶች ላንሳ። ህወሃት ለሁለት ከተሰነጠቀ በኋላ ከአስር የሚበልጡት ተባረሩ፤ የተወሰኑትም  ወደ እስር ተወረወሩና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ተፈቱ። አንዱም የህወሃት አባል ግን በፋይናንስ ችግር አልደረሰበትም። እንዲያውም እንደፈለጉ ወደ ውጪ የሚወጡና የሚገቡ ነበሩ። ሁሉም የገንዘብ ችግር አልነበረባቸውም ፤ አይኖራቸውምም። በሌላ በኩል አማራ የሆኑትን አሁን በስልጣን ላይ ያለው ደመቀ መኮነን የሱዳንን መሬት በፊርማው አሳልፎ ሰጠ በማለት ለአመታት እንዲጠላ ከዚህም የተነሳ ሌላ አማራጭ ስለሌለው ለእነርሱ ታማኝ ሆኖ እንዲኖር ከዚያ ሸርተት ቢል ግን ህዝብ ፊቱን እንዲያዞርበት የተሰራው ስራ አሁንም አማራ ከገዳቶቹ ጋር የሚኖር ደግ ህዝብ መሆኑን  ማሳያ ነው።መላኩ ፋንታን ልውሰድ አማራነቱ ያስከፈለው ዋጋ  ሙሰኛ ተብሎ ቃሊቲ መወርወር ነበር። እርሳቸው መልካም የሚባል ለውጥ ለማምጣት በመስሪያ ቤቱ ደፋ ቀና ሲሉ የሌብነቱንና ኢፍትሃዊ የሆነውን ስራ የሚያከናውኑት ምክትላቸው ገብረዋህድ ነበሩ።በምክትላቸው የነበረውን የሌብነት ሰንሰለት ቆጥሮ መጫረስ የማይቻል ቢሆንም ሁሉም የህወሃት አባላት በመሆናቸው የደረሰባቸው አንዳች ችግር አልነበረም። መላኩ ግን አማራ ነበር።ቤተሰቡ በችግር ተሰቃየ።

ሌሎችንም በየጊዜው ከመንግስት መስሪያቤቶችና ከሃገር መከላከያ የሚቀነሱ አማራ ሲቭልም ሆነ ወታደራዊ ሙያተኞች እጣ ፋንታቸው ስቃይ በተሰቦቻቸው መበተን ነበር። በእስር ቤቶች የተሰቃዩትንም አማሮች ከእኛ ከአማራው ማህበረሰብ በተጨማሪ ሌላውም እየተገነዘበ ያለበት ጊዜ ላይ ነን። በመሆኑም አሁን ጠላቶቹን በትክክል የተረዳ ትንኮሉንም ከስር መሰርቱ የተገነዘብ አማራ ማህበረሰብ ተፈጥሯል። ችግሮቻችንን በአስፈላጊው መጠን ስላወቅናቸውና ስለተረዳናቸዉም ወደ መፍው ት ሄው ተቃርበናል። በአማራው ላይ የተፈጸመውን ግፍ በመሪነት ህወሃት የሚመራው ኢህ አዴግ  ቢያስፈጽመውም እንድ ግለሰብ ግን ሟቱ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዘናዊ መሃንዲሱ ነበር። በፓርራማ  በማን አለብኝነትና በትእቢት ስለ ጉራ ፈርዳ ተፈናቃይ አማሮች ሲጠየቅ አካባቢው ምስራቅ ጎጃም መስርቅ ጎጃም ስለሸተተ ነው በማለት ተዘባበተ።  አሁን መላው የአማራ ህዝብ የተፈጸመውን የዘር ማጽዳትና እየተደረገ ያለውን እያንዳንዱን ደባ ተረድቶታል።  ትናንትና አገስት ሃያ አንድ ቀን መቀሌ የሰማእታት አዳራሽ በተደረገ የመልስ ስድስተኛ አመት ሙት አመት መታሰቢያ የቀጥታ ስርጭት ላይ ለብዙ አመታት በፓርላማ የህግ  ጉዳዮች ሰብሳቢ የነበረው አስመላሽ ባደረገው ንግ ግር

ትግራይም ሆነ ኢትዮጵያ እንደ መለስ ያለ መሪ መተካት አልቻሉም ፣አይገኝምም  አለ። ልክ ነው፤ ከእንግዲህ እንደመለስ በድብቅ በመዋቅር በመጠቀም የአማራን ዘር ለማጥፋት ሃገሪቱን የሚመራ ዘረኛ ሰው ወደፊት  አይመጣም ፤ ምክኛ ቱም አሁን አማራው ጠላቶቹን አውቋቸዋል። ቢያንስ አጥፊዉን አጥፊ ነው የሚልበት የእውቀት ደረጃ ላይ ደርሷል።  አሁን ጠላቶቹን በሚገባ የተረዳ አማራ ተፈጥሯል።